# ኖርናት

ሕይወት አለን ብለን በልዩነት ሞተን

በጥርጣሬ ሃፍረት ሆድ ለሆድ ተሻክረን

ባለመተባበር በመናናቅ ባክነን

አንዳችን በሌላወ በወንጀል ተካስሰን

እርስ በርሳችነ ልብ ለልብ ተቁሰለን

ለነፍሲያና ሽይጣን እጅግራችን ሰጥተን

ኖርናት ኢማን አለን ብለን

አለን እያልን የሞትን

ወደራሳችን ሳናይ የሰውን ነውር እያየን

ኖርናት በንፍቅና ነቅዘን

ህያው ሳለን እንደሌለን

## ሰለ፤እውቀት እንዲህ አሉ

እውቀት ከገንዘብ ይበልጣል ምክንያቱም ገንዘብን አንተ ትጠብቀዋለህ ዕውቀት ግን አንተን ይጠብቅሀል። ገንዘብ ለሰው ታዛዥ ነው ዕውቀት ደግሞ መሪ አስተማሪ አዛዥ ነው። ገንዘብ አካባቾች በቁማቸው የተረሱ ሲሆኑ  የዕወቀት ባለቤቶች ከዘመን ጋር ህያው ናቸው። አካላቸው ከአፈር በታች ሆኖ እንኮን ትሩፋታቸው በቀሪ ትውልዶች አዕምሮ ውሰጥ ይኖራል። ገንዘብ አላቂ ነው ዕውቀት ግን ለዘለዐለም ይኖራል።

# መልካም አርአያነት

አንድ መሃይም ወደአንድ ዓሊም ቤት ሂዶ " አንተ እርጉም ጠማማ በሽተኛ አረ እናትክን ..." በማለት ብዛቱና ይዘቱ ይህ ነው የማይባል ሰድብ እንደ ቦምብ አወረደበት በዚህ ግዜ አሊሙ

"ጥሩ ለተናገርከው ሁሉ ጀዛህን (ምንዳህን) አላህ ይክፈልህ ክፉ ለተናገርከውም አላህ ይማርህ" ሲል መለሰለት።

ሀስነል በስሪ የተባሉ ታዋቂ አሊም አንድ ሰው ክፉኛ እንዳማቸው አወቁና ጣፋጭ ተምርና አነስተኛ መልእክት አክለው ላኩለት መልእክቱም " ወዳጄ ሆይ! እንደምን ሰንብተሃል እንዳማሽኝ ባወቅኩ ግዜ ይሂንን ጣፋጭ ተምር ላኩልህ አምተሽኛል ብዬ አምቼህ ያገኘሁትን ምንዳ በዋዛ ማስነጥቅ ሞኛ ሞኝ አይደለሁም" የሚል ነበር።

## የለም

- ኢኽላሰ ከሌለ አጅር የለም
- ቢሰሚላህ ከሌለ በረከት የለም
- ኒያ ከሌለ ሰራ የለም
- ኢማን ከሌለ ተቅዋ የለም
- እሰልምና ከሌለ ጀነት የለም
- ሸሀዳ ከሌለ ኻቲማ የለም
- ጡሃራ ከሌለ ሶላት የለም
- ዘካ ከሌለ ዝናብ የለም
- መተሳሰብ ከሌለ ፍቅር የለም
- እምነት ከሌለ ጎደኝነት የለም
- መቻቻል ከሌለ ትዳር የለም
- ክእሰልምና የበለጠ ክብር የለም

ከተውባ የበለጠ ወደ አላህ የሚያቀርብ የለም
ከመልካም ሰራ የበለጠ አማላጅ የለም
ከሞት የበለጠ መካሪ የለም
ከጤና የበለጠ ያማረ ልብስ የለም
ከድህነት የበለጠ መራር ነገር የለም
ከሰው ዕዳ የበለጠ ከባድ ሸክም የለም
ከመጥፎ ጎደኛ የበለተ አሰቀያሚ ነገረ የለም
ከባዶ ተሰፋ የበለጠ ድህነት የለም
ክኢማን የበለጠ ውበት የለም
ከሽርክ የበለጠ ወንጀል የለም